# ወይ ሀገሬ

(ከሊ..ማ. አበባው ይግዛው፣ ግንቦት 2000 ዓ. ም.)

ሀገሬ ኢትዮጵያ ደጋ፣ ወይና ደጋ፣
ቆላና በረሃ እጅግ ባለጸጋ፣
ወንዞችሽ፣ ሐይቆችሽ፣ ባሕሮችሽ በሙሉ፣
ወራሪ ባልነካው ሀብት የታደሉ፣
በቁዋንቁዋ፣ በጎሳ ሳይከፋፈሉ፣
ምን አለ በጋራ ለልማት ቢውሉ።

ወይ ሀገሬ ክብሬ ኢትዮጵያዊነቴ፣
ተሸርሽሮ አለቀ፣ ደከመ ጉልበቴ።
አወይ ወገኖቼ፣ ትንሹም ትልቁ፣
የሀገርን ታሪክ፣ ባህል በሚንቁ፣
በጋጠወጦቹ እንዲህ ትሳቀቁ!?

ኧረ አገሬ! አገሬ ራስ-ጋይንት፣ ማማው ደብረ ታቦር፣
የሊቃውንት አምባ፣ የነጋሪት አገር፣
እንዴት በወያኔ፣ ታሪኩ ይደፈር!?
ወይ አገሬ! አገሬ አዲስ ዘመን! በለሳ ቋሊሳ፣ ዘሐጌና መና፣
እንዳላሳደገ ያንን ሁሉ ጀግና፣
ይጫወትበታል የወያኔ ሙና?!
አይ አገሬ! ወይ አገሬ ጎንደር! የፋሲል መዲና፣
የእነ ኢያሱ ዙፋን፣ እንዲህ አረጀና፣
በእነስም አይጠሩ፣ ሆኖ ሊቀር ወና?!
አገሬ አርማጭሆ! ፊልፊልና ተንፊል!
የጀግኖች መፍለቂያ፣ የጎበዞች ክልል!
እንደምን ይደፈር፣ በምንደኛ ምልምል?!
አይ አገሬ! ወይ አገሬ ደባት! የእነጋተው አገር! አገሬ ወገራ!
አገሬ ወፍ አርግፍ! ወልቃይት ጠገዴ! ደንሻና ሁመራ!
እንዴምን ይደፈር! በትግራ ኩታራ!?

ወይ አገሬ ጭልጋ! ወይ አገሬ ቋራ!
የአባ ታጠቅ አገር፣ የጀግኖቹ ጎራ!
አገሬ አዳኝ አገር! አገሬ መተማ!\
ለኢትዮጵያ አንድነት አካሉ እንዳልደማ፣
እንዴት በወያኔ ታሩኩ ይጋማማ!?

አይ አገሬ! ወይ አገሬ ሰሜን፣ ሰሜን አምባራስ!
የነጋሪት አገር! ባለብዙ ቅርስ!
እንዴት በኩታራ፣ክብሩ ይገሰስ?!
አገሬ ሳሃላ! ወይ አገሬ ፀለምት! አገሬ በየዳ!
ደራስጌ! ራስ ዳሽን!
እንዴት በወያኔ፣ ድንበርህ ይሸንሸን!?

ኧረ ጃሎ በሉ! ጎበዝ ጃሎ በሉ!
ምንሽር ወልውሉ! መውዜር አቀባብሉ!
ትናንትን ረስቶ፣ ባንዳው እንዳመሉ!
ተከዜን ተሻግሮ፣ ልግዛ ይላል አሉ!

ወይ አገሬ ሰሜን፣ አገሬ ወገራ!
ለጠገበው ጥይት፣ ለራበው እንጀራ፣
ይህ ነበር ታሪክህ፣ በጣም የሚያኮራ፣
በቁም ሊበላህ ነው የራበው አሞራ።

የሚመነጥረው፣ የሚጠርገው ቢያጣ፣
ጎንደርን እንደልብስ፣  ሊቀደው ጋሬጣ?!
ያ መልቲ ወያኔ፣ ይኸው ልብ አግኝቶ፣
በለስ ቀናውና በቋንቋ አዘናግቶ፣
ወልቃይት ጠገዴን፣ ደንሻና ሁመራን፣ ከጎንደር ለይቶ፣
ሰሊጥ አምርተናል፣ ይበል አፉን ሞልቶ?!
ዕንቋይ* ሲቀባጥር፣ ወልቃይት ልብ በል፣ አርማጭሆም አዳምጥ፣
ትግራይ ያበቅላል ወይ፣ አንድ አገዳ ሰሊጥ?!
ተርቦ ተጠምቶ፣ የሚቀምሰው ሲያጣ፣
ወያኔ ተከዜን፣ ተሻግሮ ሲመጣ፣
ከእንግድነት በቀር፣ መች ነበረው ጣጣ።

እኒያ ደጋጎቹ፣ አገር ዘበኞቹ፣ የሀገሬ ጀግኖች፣
ዘራቸው የት ጠፋ!
አይናውጣው ወያኔ፣ ታሪክ ሲያከረፋ!
ያባቶቹን ርስት፣ ገበሬው ሲቀማ!
ሁመራ ተመርቶ! መቀሌ ሲለማ!
ምናለ አርማጨሆ?! ምናለ ወገራ?! ይኸንን ሲሰማ?!

ለሰሚው ግራ ነው፣ እንዲህ ያለ ነገር፣
የ አርማጭሆ ሱሪ! የወልቃይት ሱሪ! የወፍ አርግፍ ሱሪ!
መች እንዲህ ነበረ!!!
"ሰሜን አርማጭሆ! ወልቃይት ጠገዴ!
ማረሻው ምንሽር! መጎልጎያው ጓንዴ!"
የሚለው ቀረርቶ፣ ውሸት ነበር እንዴ?!
"አንበሳ ተኝቶ፣ ጊደር ሸናችበት፣
ከምን ያለው ጊዜ፣ እኛ ደረስንበት?!
ያንበሳ ልጅ ሙቶ፣ የጅብ ልጅ ገነነ፣
አላሳልፍ አለ፣ ጸጉሩ እየበነነ፣"
ይባል የነበረው፣ እውን እውነት ሆነ?!

______*
ሰለሞን ዕንቋይ ለማለት ነው

ሰሜን አርማጭሆ፣ ወልቃይት ጠገዴ፣
እንዲህ እንደዋዛ፣ ስሙን ለወጠ እንዴ?!
ወገራና ሰሜን፣ አርማጭሆም አብሮ፣
ለትግራይ ጉልተኛ፣ ተከዜን ተሻግሮ፣
ገብሮ ያውቃል ወይ?! ቅመም ምጥን ሽሮ?!
የትግሬ ህዝብ ሲራብ፣ ቆርሶ ባጎረሰ፣
መሶብ ቤት ሆነና እጁን ተነከሰ!
ተፈርቶ ተከብሮ፣ ጀግኖ እንዳልኖረ!
ባይን አውጣ ወያኔ፣ ቤቱ ተደፈረ።
የወልቃይት ጎበዝ፣ የጠገዴ ጀግና፣
ቤቱ ተደፈረ፣ ቀየው ተወረረ፣ ዘመን አረጀና!!!
ያንን ጀግና ትውልድ፣ የኖረ ተፈርቶ፣
እንደምን ይስለበው?! በቋንቋ አዘናግቶ?!
እየተቀጠረ፣ እንዳልባ'ገተበት!
የሁመራን ሰሊጥ፣ ባለቤት ሆነበት?!
ወይ አገሬ! ኧረ አገሬ! አገር አጥፊው አረም፣ ባገሬ ሲስፋፋ፣
ሁሉም ተዳከመ፣ የሚያርመው ጠፋ!
የጊዜ ጉዳይ ነው፣ እኔ አልቆርጥም ተስፋ!
አገሬ ነው የሚል፣ ኢትዮጵያዊ ሁሉ፣
ጥቃቱ ይሰማው፣ ሲቆረስ አካሉ!

ወይ አገሬ! ኧረ አገሬ!
ለሱዳን ሲከለል፣ መሬቱ ተቆርሶ፣
ዘንድሮ አርማጭሆ፣ በወየታው ለቅሶ፣
እንደዚህ ያዜማል፣ መልሶ መላልሶ።
"አረጀ አርማጭሆ! አረጀ አብደራፊ!
ይቀደድ ጀመረ፣ እንደጨርቅ እራፊ!"
አንተ ክፉ ዘመን፣ ነፍስህን አይማረው!
የወንዶቹን አልጋ፣ ትንኙ ወረረው!
የወንዶቹን ማሳ፣ የህዝቡን-አጽመ ርስት፣
ሱዳን አርማጭሆን፣ ከብት አሰማራበት!?
ዘብ ሆነን እንዳልኖርን፣ በጠረፍ ጥበቃ!
በራሳችን ሰዎች፣ እንዴት እንጠቃ?!
ገደብ ይበጅለት፣ ይኸ ነገር ይብቃ!

"ከአባቴ ባድማ፣ ፍግ አታፍሱበት!
እሳቱ ቢጠፋ! ረመጡ አለበት!"
ሁመራ መተማ፣ መተማ ሁመራ፣
መች ተደፍሮ ያውቃል፣ በጠላት ወረራ?!
ዛሬ አስጠቃን እንጅ፣ እኩይ ባላጋራ!

ሱዳንስ ያውቀናል፣ በቅርቡም በሩቁ፣
ይብላን ለነሀጎስ፣ ለነትግል ብርቁ!!!
ከዛሬ በስተቀር፣ ነገን ለማያውቁ!

“ውሽልሽል ነው! ውሽልሽል ነው እርቁ!
አውድማው ይለቅለቅ! በሮቹም አይራቁ!
እንኳን ከቀያችን! ሰተት ብሎ ገብቶ!
ከሩቁ ያውቀናል፣ ሱዳን መች ዘንግቶ!
የጀግኖቹን ቀየ፣ የህዝቡን አጽመ-ርስት፣
እንዴት እናያለን፣ ሱዳን ሲኮስበት!?

“የትግራይ ምንደኞች፣ እየተሳሳቡ፣
ግዙን ብንላቸው፣ ሊሸጡን አሰቡ!
ኢትዮጵያዊ ስማ! ልብህ አያመንታ!
መሀል ዳር ይሆናል! ዳሩ ከተፈታ!”

ፉከራ፡ ኧረ ቆሉብን! ኧረ ፈጩብን!
እንጠብቃልን እስኪያቦኩብን!
ከዋለ ካደረ፣ አይሰማ የለ!
ድርቡሽ እንደገና፣ ቋራን አቃጠለ!?
የአርማጭሆን መሬት፣ ድርቡሽ ተካፈለ?!
ማሕበረ-ስላሴን፣ ገዳሙን ከለለ!?

ምን ትጠብቃለህ?! ከወያኔ መንጋ?!
አካልህን ሲያፈርሰው! እንደ ደዌ ስጋ?!
ሰሜን አርማጭሆ፣ ወልቃይት ጠገዴ፣ አርግዟል! አርግዟል!
አልተገላገለም! ገና ምጥ ተይዟል!
ፈራን አላልናቸው?! እርዱን አላልናቸው?!
እነርሱን እንደዚህ፣ ምን አስቀዘናቸው?!
ለሱዳን ጥብቅና፣ ማነው ያቆማቸው?!
“ተላላ ነው አገር! ተላላ ነው! ይጓዛል እንደ ሰው!
በየበሩ ቆሞ! ጀግና ታልመለሰው!!!”